በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ጥር 4 ቀን 2011
አዲስ አበባ
መግለጫ

# 61ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት ጥር 4 ቀን 2011 ባካሄደው 61ኛ መደበኛ ስብሰባ በሁለት ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በማዕድን ግብይት ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን የሁሉንም አይነት ማዕድን ግብይት ለማስፋፋት፣ ሕጋዊ ስርአት ለማስያዝና፣ ለመቆጣጠር የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ የሚያስፈልግ በመሆኑና የማዕድን ግብይት ስርአትን ዘመናዊ በማድረግ ዘርፉ ለኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ የሚያስችል የግብይት ስርአት ለመፍጠር የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡
2. ምክር ቤቱ በመጨረሻ የተወያየው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ለማቋቋም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ ዜጎች በየደረጃው በሚካሄድ ነፃ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ ምርጫ በማካሄድ በመረጧቸው ተወካዮች አማካኝነት ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ስልጣናቸውን በተግባር እንዲያውሉ ለማድረግ ነፃ የምርጫ አስፈጻሚ አካል አስፈላጊ በመሆኑና በኢትዮጵያ ዲሞክራሲን ለማጠናከር ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን ከማንኛውም አካል ነፃ አድርጎ በማደራጀት ፍትሃዊ፣ ተአማኒና ሰላማዊ ምርጫ ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ ጠቅላይ አቃቤ ህግ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ም/ቤቱ በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየበት በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል አዋጁን ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

//